# መጽሐፍ ቅዱስ

## የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

፨ ፨ ፨ ፨ ፨

**ዲጂተል ኤዲሽን ፲፱፻፺፱**
**በዲርክ ሮክማንና ፍሬዘውድ ተክሉ**
**DIGITAL EDITION BY DIRK RÖCKMANN AND FREZEWD TEKLU 2006**
**ETHIOBIBLE MINISTRIES - WWW.ETHIOBIBLE.ORG**
Release 1.0

## የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር

መጀመሪያ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ ።

**COPYRIGHT STATEMENT:**
DIGITAL EDITION OF THE REVISED AMHARIC BIBLE (2006) | PRINTED VERSION BY UNITED BIBLE SOCIETIES (C)1962| E-TEXT IN TRANSLITERATED SIL-ASCII FORMAT BY LAPSLEY/BROOKS FOUNDATION 1994 | UNICODE UTF-8 TRANSFORMATION AND XML-TAGGING BY DIRK RÖCKMANN 2003 | XSLT-TRANSFORMATION AND READER FORMAT BY DIRK RÖCKMANN 2006 | WITH KIND PERMISSION OF THE BIBLE SOCIETY OF ETHIOPIA | EVERY NON-COMMERCIAL WORK USING THIS DATA IN ANY FORM MUST FULLY INCLUDE THIS COPYRIGHT STATEMENT! | EVERY COMMERCIAL USE OF PARTS OR THE COMPLETE DATA IN ANY FORM NEEDS WRITTEN PERMISSION OF THE BIBLE SOCIETY OF ETHIOPIA AND DIRK RÖCKMANN (WWW.NT-TEXT.NET,WWW.ETHIOBIBLE.ORG)! ALL RIGHTS RESERVED!

# የዮሐንስ መልእክት 3

## ምዕራፍ 1

1፤ ሽማግሌው በእውነት እኔ ለምወደው ለተወደደው ለጋይዮስ። 2፤ ወዳጅ ሆይ፥ ነፍስህ
እንደሚከናወን፥ በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ። 3፤
ወንድሞች መጥተው አንተ በእውነት እንደምትሄድ ስለ እውነትህ ሲመሰክሩ እጅግ ደስ
ብሎኛልና። 4፤ ልጆቼ በእውነት እንዲሄዱ ከመስማት ይልቅ የሚበልጥ ደስታ የለኝም።
5፤ ወዳጅ ሆይ፥ ምንም እንግዶች ቢሆኑ፥ ለወንድሞች በምታደርገው ሁሉ የታመነ
ሥራ ትሠራለህ፥ እነርሱም በማኅበር ፊት ስለ ፍቅርህ መሰከረዋል፤ 6፤ ለእግዚአብሔር
እንደሚገባ አድርገህ በጉዞአቸው ብትረዳ መልካም ታደርጋለህ፤ 7፤ ከአሕዛብ አንዳች
ሳይቀበሉ ስለ ስሙ ወጥተዋልና። 8፤ እንግዲህ ከእውነት ጋር አብረን እንድንሠራ እኛ
እንዲህ ያሉትን በእንግድነት ልንቀበል ይገባናል። 9፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን ጻፍሁ፤ ዳሩ
ግን ዋናቸው ሊሆን የሚወድ ዲዮጥራጢስ አይቀበለንም። 10፤ ስለዚህ፥ እኔ ብመጣ፥
በእኛ ላይ በክፉ ቃል እየለፈለፈ የሚያደርገውን ሥራውን አሳስባለሁ፤ ይህም ሳይበቃው
እርሱ ራሱ ወንድሞችን አይቀበልም፥ ሊቀበሉአቸውም የሚወዱትን ከልክሎ ከቤተ
ክርስቲያን ያወጣቸዋል። 11፤ ወዳጅ ሆይ፥ በጎ የሆነውን እንጂ ክፉን አትምሰል። በጎ
የሚያደርግ ከእግዚአብሔር ነው፤ ክፉን የሚያደርግ ግን እግዚአብሔርን አላየውም። 12፤
ለድሜጥሮስ ሁሉ ይመሰክሩለታል፥ እውነት ራስዋም ትመሰክርለታለች፤ እኛም ደግሞ
እንመሰክርለታለን፥ ምስክርነታችንም እውነት እንደ ሆነ ታውቃላችሁ። 13፤ ልጽፍልህ
የምፈልገው ብዙ ነገር ነበረኝ፥ ዳሩ ግን በቀለምና በብርዕ ልጽፍልህ አልወድም፤ 14፤
ነገር ግን ወዲያው ላይህ ተስፋ አደርጋለሁ፥ አፍ ለአፍም እንነጋገራለን። 15፤ ሰላም
ለአንተ ይሁን። ወዳጆች ሰላምታ ያቀርቡልሃል። ወዳጆችን በየስማቸው እየጠራህ ሰላምታ
አቅርብልኝ።